# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# በግ ጠባቂው ልጅ ዳዊት፡፡

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



ከረዥም ጊዜ በፊት ፣ በእስራኤል ንጉስ በሳኦል ዘመን ፣ ዳዊት የሚባል ትንሽ ልጅ ፣ የአባታቸውን በግ ይጠብቁ የነበሩትን ሰባት ወንድሞቹን ይረዳቸው ነበረ፡፡ ምንም ታናሽ ቢሆን ፣ ዳዊት እግዚአብሔርን የሚወድና የሚያምን ጠንካራና ብልህ ልጅ ነበረ፡፡ እርሱም ፣ ቤቴልሔም በሚባል መንደር ይኖር ነበረ፡፡



አንድ ጊዜ አንበሳ ትንሽዬን ጠቦት ሊበላ ፈልጎ መንጋውን ሲያጠቃ ፣ ታናሹ ዳዊት አጥቂውን አጠቃው፡፡ ጠጉራሙን አውሬ ጢሙን ይዞት ገደለው፡፡ ዳዊትም እግዚአብሔር እንደረዳው አወቀ፡፡



3

ንጉስ ሳኦል እግዚአብሔርን እጅግ በድሎት ነበረና ፤ ሳሙኤል ፤ የእግዚአብሔር ነብይ እጅግ አዝኖ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ሳሙኤልን አለው ፤ “ስለ ሳኦል እስከመቼ ታለቅሳለህ?” “እኔ ወደ እሰይ እልክሃለሁ ፤ ከልጆቹ መሀከል ንጉስ እንዲሆን ሰጥቼሃለሁና”፡፡ እሰይ የዳዊት አባት ነበረ፡፡



4

ምንም እንኳን ሌላ ንጉስ ሊፈልግ እንደሆነ ሲያውቅ ንጉስ ሳኦል ሊገድለው እንደሚችል ሳሙኤል ቢያውቅም፣ ነብዩ እግዚብሔርን ታዘዘ፡፡



5

ሳሙኤል ሲደርስ ፣ እሰይ በሳሙኤል ፊት የሚያሳልፋቸውን ሰባት ልጆች አዘጋጅቶ ነበረ፡፡ ሳሙኤልም ለእሰይ አለው ፣ “አግዚአብሔር እነዚህን አልመረጣቸውም.” ታናሹ ልጅ ዳዊት ብቻ ነው የቀረው፡፡ እርሱ ከበጎቹጋ ውጪ ነው ያለው፡፡ ዳዊትን ወደ ውስጥ አመጡት ፡፡ ጌታም አለ ፣ “አስነሳውና ቀባው ፤ የሚቀባው ይሔ ነውና፡፡”



6

በሳኦል ቤተመንግስት ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል ተለየውና ሳኦል እጅግ የሚረሽ ሰው ሆነ፡፡ አገልጋዮቹም የሳኦልን አዕምሮ ጥሮ ሙዚቃ ሊያረጋጋ እንደሚችል አሰቡ፡፡ ከእነርሱም መካከል አንዱ ፣ በገናውን ጥሩ አድርጎ የሚጫወት ወጣት ያውቅ ነበረ፡፡ ያ ወጣት ልጅ ማን ሊሆን እንደሚችል ልትገምት ትችላለህ ?



7

የዳዊትም ሙዚቃ ፣ ሳኦልን ያረጋጋ እና በትክክሉም ማሰብ እንዲችል ይረዳው ነበረ፡፡ ሳኦልም ዳዊት በንጉሱ አግልግሎት ዙሪያ እንዲያስቀረው ብሎ እሰይን ይለምነው ነበረ፡፡ ሳኦልም በፍርሃት ድባቴ በሚጠቃበት ጊዜ ሁሉ ፣ ዳዊት በገናውን ይጫወትለት ነበረ፡፡ እርሱም ይረዳው ነበረ፡፡



8


ዳዊት ወደቤቱ ከሄደ በኋላ ፣ ሳኦል ከፍልስጤማዊያንጋ ፍልሚያ ውስጥ ገባ። የዳዊት ወንድሞች በሳኦል ሰራዊት ውስጥ ሆነው ይዋጉ ነበረ። እሰይም ለልጆቹ ምግብን እንዲያደርስና እነርሱ ምን ላይ እንዳሉ እንዲያይ ልጁን ዳዊትን ላከው።
9
ጎልያድ የሚባል እጅግ ግዙፍ ፍልስጤማዊ የእስራኤልን ወታደር ሁሉ ያስፈራራ ነበረ።
10
ጎልያድም እንዲህ እያለ ይጮህ ነበረ ፤ “ለራስህ ሰውን ምረጥ ፤ ከእኔምጋ እንዲወርድ አድርገው።” እርሱ ከእኔጋ መፋለምና መግደል የሚችል ከሆነ ፣ እኛ አገልጋዮችህ እንሆናለን። ነገር ግን እኔ እርሱን ከገደልኩት ፣ አንተ የእኛ አገልጋይና ሆነህ ታገለግለናለህ።” የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ፣ ያንን ግዙፍ ሰው ሲያዩት ፣ ከእርሱ ይሸሹና ይንቀጠቀጡ ነበረ።
11
ከዚያም ዳዊት ለሳኦል እንዲህ አለው ፤ “በእርሱ ምክንያት የማናችሁም ልብ አይውደቅ ፤ የእናንተ አገልጋይ ይሔድና ከእዚህ ፍልስጤማዊጋ ይፋለማል።” ሳኦል ዳዊትን የጦር እቃ ሊያለብሰውና ሰይፍ ሊያስታጥቀው ፈለገ። በምትኩ ፣ ዳዊት ወንጭፉን በመያዝ ፣ አምስት ድንጋዮችን ከምንጭ ዳር አነሳ።
12
ጎልያድም ያ ትንሹ ዳዊት የጦር ዕቃ እንኳን እንዳልያዘ ባየ ጊዜ ሳቀ። እንዲህም ብሎ አፌዘ ፣ “ስጋህን ለሰማይ ወፎችና በምድርም ላሉ እንስሳት እሰጣለሁ።” ዳዊትም መለሰለት “በጌታ ስም እመጣብሃለሁ።” “በዚህች ቀን እግዚአብሔር በእጄ አሳልፎ ይሰጥሃል። ውግያው የእግዚአብሔር ነውና።”
13
ከዚያም ዳዊት በቀጥታ ወደ ጎልያድ እየሮጠ ሔደ። እየሮጠም ሳለ፣ ከወንጭፉ አውጥቶ አንድ ድንጋይ ወደ ጎልያድ ወረወረ - በቀጥታ በጎልያድ አናት ላይ አነጣጥሮ። ጎልያድም ወደቀ።
14

ዳዊትም በፍጥነት የጎልያድን ሰይፍ አውጥቶ
ጭንቅላቱን ቆረጠው፡፡ ፍልስጤማዊያንም ጎልያድ
እንደሞተ ባዩ ሰዓት ፣ የራሳቸውን ሕይወት ለማትረፍ
ሩጫቸውን ቀጠሉ፡፡



15

ንጉስ ሳኦል ይሔኛው ዳዊት ፣ በገና እየደረደረ ይረዳው የነበረው ያ ራሱ
ዳዊት እንደነበረ አላወቀም ነበረ፡፡ እርሱ ራሱ ዳዊትን በሰራዊቱ ምትክ
አስቀመጠው ፤ ከዚያም ሰው ሁሉ የዳዊትን
ድል እጅግ ሲያወድስ ተመልክቶ ቅንዓት
አደረበት፡፡ ሳኦልም ለራሱ እንዲህ አለ “አሁን
ከንግስና ውጪ ምን ቀረው?” ከዚያም ቀን
በኋላ ሳኦል ዳዊትን በአይነ ቁራኛ
ይከታተለው ጀመረ፡፡



16

እንደገናም ፣ የንጉስ ሳኦል አዕምሮ ይረበሽ ጀመረ፤ ስለዚህም ዳዊት
ሊያረጋጋው ፈልጎ ሙዚቃ ይጫወት ነበረ፡፡ ሳኦልም ሶስት ጊዜ ጦሩን ዳዊት
ላይ ይወረውር ነበረ፡፡ ነገር ግን ዳዊት ሁሉንም ጊዜ ያመልጠው ነበረ፡፡

ሳኦል ዳዊትን
ይፈራው ነበረ ፤ ምክንያቱም
እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደነበረ
አውቆ ነበረና ፤ ነገር ግን
ዳዊት ከሳኦል ይሸሽ ነበረ፡፡



17

ነገር ግን የሳኦል ልጅ ዮናታን ዳዊትን እንደ ወንድሙ አድርጎ ይወደው
ነበረ፡፡ ዳዊትን እንዲህ ሲል አስጠነቀቀው “አባቴ ሳኦል አንተን
ሊገድልህ ይፈልግሃል፡፡” ስለዚህም ፣ ዳዊት አመለጠ፡፡ የሳኦል
ሚስትም ዳዊት በሌሊቱ መካከለኛ ሰዓት ከአልጋው በመስኮቱ
በኩል ወርዶ እንዲሄድ ፣ ከአልጋው ስር ምስል ታስቀምጥ
ነበረ፡፡ የሳኦልም ሰዎች በጠዋት ወደ ቤቱ
ሲመጡ ፣ ዳዊት አምልጦ ይሔድ ነበረ፡፡



18

ዳዊት ከሳኦል ርቆ መሸሽ ነበረበት፡፡ ይሄንን ከማድረጉ በፊት፣ እርሱና ዮናታን
በአንድነት ኪዳን አደረጉ፡፡ እርስ በእርስ እንደሚረዳዱም ቃል ተገባቡ፡፡
በአሳዛኝ ሁኔታ፣ ሁለቱ ጓደኛማቾች ደህና ሰንብት ተባባሉ፡፡ ዳዊት ከሳኦል
ወታደሮች ፍርሃት ሸሽቶ መኖር የሚችልበትን ቦት ይፈልግ ነበረ፡፡



19

በግ ጠባቂው ልጅ ዳዊት፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል**
**በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ሳሙኤል 16-20

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

20



# መጨረሻ

19

60



ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16